ግብጽ አረብ ሪፐብሊክ ረቢዕ ሳኒ 28/1443 ሂ.
አውቃፍ ሚኒስቴር ዲሴምበር 3/2021 ግ.

# የእስልምና ስልጣኔ ሰብአዊነት

ምስጋና ሁሉ በተከበረው መጽሐፉ

{يَا أَيُّهَا النَّاسُ اتَّقُوا رَبَّكُمُ الَّذِي خَلَقَكُمْ مِنْ نَفْسٍ وَاحِدَةٍ}
ለአለው ለዓለማቱ ጌታ ለአላህ ይገባው፡ የአንቀጹዋ ትርጉም፡

(እናንተ ሰዎች ሆይ! ያንን ከአንዲት ነፍስ (ከአዳም) የፈጠራችሁን... ጌታችሁን ፍሩ፡፡) ማለት ነው፡፡
አጋር የሌለው ብቸኛ አላህ እንጅ የሚገዙት አምላክ እንደሌለ እመስክራለሁ፡፡ ሰይዳችንና ነብያችን ሙሐመድ የእሱ ባሪያና መልእክተኛ በመሆናቸውም እመሰክራለሁ፡፡ ጌታዬ ሆይ! የምህረት እዝነትህን፣ ሰላምህንና በረከትህን በርሳቸው፣ በቤተሰቦቻቸው፣ በባልደረቦቻቸውና እስከ እለተ ቂያማ ድረስ በመልካሙ መንገድ ለተከተሏቸው አውርድ፡፡
ከዚህም በመቀጠል

የእስልምና እምነት በሰብአዊ እስቶቹ የምልኡነት ቆንጮ የደረሰን ስልጣኔ አዋቅሯል፡፡ ለሰው ልጅ የፍቅር፣ የወንድምነት፣ የፍትህና የእኩልነት ጎዳናንም ቀይሷል፡፡ ይህውም ሰብሳቢ እንጅ በታኝ ያልሆኑ ገንቢ እንጅ አፍራሽ ያልሆኑ የስልጣኔና የሥነ ምግባር ደንቦችን በመዘርጋት ነው፡፡ በዚህም በመላ ነዋሪዎች ዘንድ ጸጥታና ሰላም እንድሁም ደግ ነገር ሁሉ ይሰፍናል፡፡

የእስልምና ስልጣኔ ይህን ሰብአዊነት የቀሰመው ከቅዱስ ቁርኣንና ከነብያዊ ፈለጎች ነው፡፡ እነዚህ ምንጮች ተላላቅ የሰብኣዊ ደንቦችን ሁሉ አካተዋል፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ ይላል፡

**{يَاأَيُّهَا النَّاسُ إِنَّا خَلَقْنَاكُمْ مِنْ ذَكَرٍ وَأُنْثَى وَجَعَلْنَاكُمْ شُعُوبًا وَقَبَائِلَ لِتَعَارَفُوا إِنَّ أَكْرَمَكُمْ عِنْدَ اللَّهِ أَتْقَاكُمْ إِنَّ اللَّهَ عَلِيمٌ خَبِيرٌ}**

(እናንተ ሰዎች ሆይ! እኛ ከወንድና ከሴት ፈጠርናችሁ፡፡ እንድትተዋወቁም ጎሳዎችና ነገዶች አደረግናችሁ፡፡ አላህ ዘንድ በላጫችሁ በጣም አላህን ፈሪያችሁ ነው፡፡ አላህ ግልጽን ዐዋቂ ውስጥንም ዐዋቂ ነው፡፡)

የሰው ልጅ ክብሩን ያገኘው ጎሳውን፣ ቀለሙን ወይም ሃይማኖቱን መነሻ ሳያደርግ ከአላህ ዘንድ በተቸረ መልኩ ነው፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ ይላል፡

**{ وَلَقَدْ كَرَّمْنَا بَنِي آدَمَ}**

(የአደምንም ልጆች በእርግጥ (ከሌላው ፍጡር) አከበርናቸው፡፡)

ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) እንድህ ይላሉ፡ (ሁላችሁም ከአደም ናችሁ፡፡ አደምም ከአፈር ነው)፡፡ በነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) አጠገብ አስከሪን ባለፈ ጊዜ ለሱ አክብሮት ከተቀመጡበት ተነሱና ቆሙ፡፡ ያን ጊዜም ሰዎች የአይሁድ አስከሪን ነውኮ አሏቸው፡፡ እርሳቸውም (እርሱ ነፍስ አይደለምን) አሉ፡፡

ከእስልምና ስልጣኔ ሰብአዊነት ገጽታዎች አንዱ መላ ምትን በማይቀበል ሁኔታ ግልጽ በሆነ መልኩ የሃይማኖት ነፃነትን በደንቡ ማካተቱ ነው፡፡ እንድሁም የስርአተ አምልኮት ነፃነት፣ የማንኛውም ቤተ ጸሎት ጥበቃ፣ ሁሉንም የማስገደድና የማስሸበር ገጸታዎችን አለመቀበል የሚሉት ደንቦች በእስልምና አምነት ህግጋት ይካተታሉ፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ ይላል፡

**{لَا إِكْرَاهَ فِي الدِّينِ}**

(በሃይማኖት ማስገደድ የለም፡፡) እንድሁም እንድህ ይላል፡

**{وَلَوْ شَاءَ رَبُّكَ لَآمَنَ مَن فِي الْأَرْضِ كُلُّهُمْ جَمِيعًا أَفَأَنتَتُكْرِهُالنَّاسَحَتَّىيَكُونُوامُؤْمِنِينَ}**

(ጌታህም በሻ ኖሮ በምድር ያሉት ሰዎች ሁሉም የተሰበሰቡ ሆነው ባመኑ ነበር፡፡ ታዲያ አንተ ሰዎችን አማኞች እንዲኾኑ ታስገድዳለህን) አሁንም እንድህ ይላል፡

**{فَذَكِّرْ إِنَّمَا أَنتَ مُذَكِّرٌ * لَّسْتَ عَلَيْهِم بِمُصَيْطِرٍ}**

(አስታውስም፤ አንተ አስታዋሽ ብቻ ነህና፡፡) በድጋሜም እንድህ ይላል፡

**{ِنْ عَلَيْكَ إِلا الْبَلاغُ}**

(ባንተ ላይ ማድረስ እንጅ ሌላ የለብህም፡፡)

ከእስልምና ስልጣኔ ገጽታዎች በከፍተኛ መልኩ ሰብአዊ ናቸው የሚባሉት፡ ለደካማ ማዘን፣ አረጋዊያንን ማክበር፣ በታማኝነት ለሚታትሩ ወገኖች ምንም ያለማጓደል መበትቻውን መስጠት የሚሉት ናቸው፡፡

ነብያችን (ሰ.ዐ.ወ.) እንድህ ይላሉ፡ (ይህን ህዝብ አላህ የሚረዳው በደካሞቹ ጸሎትና በተማኝነታቸው ነው)፡፡ እንዲሁም በሌላ ሐዲስ እንድህ ይላሉ፡ ( ከኛ ለትንሻችን ያላዘነና ትልቃችነንም ያለከበረ ከኛ አይደለም)፡፡ (ከርሳቸው አላህ ይውደድና) ዑመር ኢብን አልኸጣብ ከመጽሐፍ ባለቤቶች አንድ አረጋዊ በሰዎች ደጃፍ እየለመነ ባዩ ጊዜ በሸበትህ የሚገባህን አላደረግንልህም በእርጅናህም መብትህን አልጠበቅንም አሉና ከመንግስት ግምጃ ቤት የሚበቃው ወጭ እንድወሰንለት አዘዙ፡፡

ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) እንድህ ይላሉ፡ ( አዛኞች አራህማን ያዝንላቸዋል፡፡ በምድር ለአለው ፍጥረት እዘኑ በሰማይ ያለው ፈጣሪ ያዝንላችኋልና)፡፡

****

ምስጋና ሁሉ ለአለማቱ ጌታ ለአላህ ይገባው፡፡ የእዝነት መህረትና ሰላም የነብያትና የመልክተኞች መደምደሚያ በሆኑት በሰይዳችን ሙሐመድ (ሶ.ዐ.ወ.) በቤተሰቦቻቸውና በመላ ባልደረቦቻቸው ይውረድ፡፡

የእስልማና ስልጣኔ ሰብኣዊነት ከሰው ልጆች መካከል በአለው ግንኙነት ወሰን ብቻ የተገደበ አይደለም፡፡ ይልቁንም ከእንስሳት ጋር ያለውንም ግንኙነት ያካትታል፡፡ ለዚህም ዋነኛ መረጃ የሚሆነው ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) ከእለታት አንድ ቀን ከአንሷሮች ወገን በሆነ አንድ አትክልት በገቡበት ወቅት አንድ ግመል ባለቤቱ የሚፈጽምበትን ስቃይ በመግለጽ በእዘን እየጮኸ እንባውን ሲያፈስ ስሜታቸው እጅጉን ተነክቶ በእዝነት ጆሮ ግንዶቹን ሲዳስሱለት ጸጥ ማለቱ ነው፡፡ በዚያን ግዜም እንድህ አሉ፡ ( የዚህ ግመል ባለቤት ማነው) አንድ ከአንሷሮች ወገን የሆነ ወጣት ቀረበና የኔ ነው የአላህ መልክተኛ ሆይ! አለ፡፡ እርሳቸውም (በዚህ እንሰሳ እሱን ለአንተ ንብረት አድርጎ የሰጠህን ጌታ አላህን አትፈራምን እሱ አንተ እንደምታስርበውና እንደምታደክመው ስሞታ ነገሮኛል) አሉ፡፡

እንድሁም ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) ከእለታት አንድ ቀን አንድ ድንቢጥ ብጤ ወፍ ሁለት ጫጩቶች ጋር ስትሄድ ጫጩቶቹዋ ተይዘውባት አንዳዘነች አዩ፡፡ በዚህን ጊዜም እንድህ አሉ፡ (ማነው ይህችን ወፍ ልጆቹዋን ወስዶ እንድህ ያሳዘናት በሉ ልጆቹዋን መልሱላት)

መላው የሰው ልጅ በአሁኑ ወቅት በተለያዩ ዘመናት የእስልምና ስልጣኔ ከሌሎች ስልጣኔዎች የተለየባቸውንና ከላይ የተጠቀሱትን ሰብኣዊ እሴቶችና መርሆች ተግባራዊ ማድረግ እጅግ በጣም ያስፈልጋቸዋል፡፡

ጌታችን ሆይ! ሀገራችን ግብጽንና መላው የዓለም ሀገራትን ድሎትና ለጋስነት የበዛበት አድርግልን፡፡

አሚን